ማስታወቂያ




ኢትዮጵያ

# በሲዳማ ሶስት አካባቢዎች 34 ሰዎች መሞታቸውን እማኞች እና ሲአን ገለጹ

**በደቡብ ክልል ሲዳማ ዞን ሶስት አካባቢዎች የሞቱ ሰዎች ቁጥር 34 መድረሱን የአካባቢው ነዋሪዎች እና ተቃዋሚው የሲዳማ አርነት ንቅናቄ ፓርቲ ገለጹ። አንድ የዓይን እማኝ በሁላ ወረዳ ሀገረ ሰላም ከተማ 14 ሰዎች ሲገደሉ መመልከታቸውን ተናግረዋል።**




ማንነታቸው እንዳይገለጽ የጠየቁ የሁላ ነዋሪ ለዶይቼ ቬለ እንደተናገሩት ከትላንት በስቲያ አርብ ከቀኑ 10 ሰዓት ገደማ ጥያቄያቸውን ለማቅረብ ወደ ፌደራል ፖሊሶች የሄዱ የከተማይቱ ነዋሪዎች ተኩስ ተከፍቶባቸዋል። በጥይት የተመቱት አብዛኞቹ ወጣቶች መሆናቸውን የተናገሩት የዓይን እማኙ ወዲያውኑ ወደ ሁላ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል ቢወሰዱም አስራ አራቱ ህይወታቸው ማለፉን ገልጸዋል።

“ከትላንት ወዲያ እዚህ ሆስፒታል አስገብተው ያወጧቸውን ወደ 14 ሰዎች ነው ያየሁት። ያው እነርሱ የሞቱት በፌደራል ፖሊስ ነው። ግጭት አልነበረም። ህዝቡ ለመጠየቅ ወደ እነርሱ ሲሄድ ወደ ህዝቡ ተኮሱ። በዚያ ሰዓት በመትረየስ ሲመቱ አስሩ በአንድ ጊዜ ወደቀ። ከዚያም [ሌሎችም] ወደቁ። አንዳንዶቹ ቆሰሉ። ወደ 14 የሆኑት ሞቱ” ብለዋል የዓይን እማኙ።

የፌደራል ፖሊስ አባላት ሐሙስ ምሽት ወደ ሀገረሰላም መግባታቸውን የሚናገሩት ነዋሪው በነጋታው አንድ ወጣት ልጅ መገደሉን ተከትሎ ነዋሪዎች ለጥያቄ መሄዳቸውን ለዶይቼ ቬለ አስረድተዋል። በከተማይቱ ፖሊስ ጣቢያ ሰፍረው የነበሩት ፖሊሶች ነዋሪውን ሲመለከቱ መተኮሳቸውን ገልጸዋል።

“በዚህ የሆኑ ልጆች ሞተው ‘እኛ ሰላማዊ ነን። የጠየቅነው ጥያቄ አልተመለሰም። እኛ የፈለግነው ክልሉ ባለፈው የተጠየቀው እርሱ አልተመለሰም። እኛ ውጊያ አልፈልግንም። እናንተ በእኛ ላይ ለምንድነው የምትተኩሱት’ እያሉ ለመጠየቅ ሲሄዱ ነው። ፖሊስ ጣቢያ አካባቢ ነበር። ባጃጆች የሚቆሙበት አለ። እነርሱም የቆሙበት እዚያ ነበረ። እዚያ ሆነው ሲተኩሱ እኔ እዚህ ዳር ላይ ስለሆንኩ ይታያል” ሲሉ አብራርተዋል።

በሁላ የሞቱ ሰዎች የቀብር ስነ ስርዓት ትላንት እና ዛሬ መፈጸሙን የከተማይቱ ነዋሪ ተናግረዋል። በሀገረ ሰላም ዛሬ የተረጋጋ ሁኔታ እንደሚስተዋል እና በአካባቢው አሁንም የፌደራል ፖሊሶች እንዳሉ ጠቁመዋል። በአርቡ ተኩስ የቆሰሉ ሰዎች ወደ ተለያዩ ቦታ መወሰዳቸውን የሚገልጹት የዓይን እማኙ ትክክለኛ ቁጥራቸውን ግን አላውቅም ብለዋል።




ዶይቼ ቬለ የሀገረ ሰላም ከተማ ባለሥልጣናትን በጉዳዩ ላይ ለማነጋገር ያደረገው ተደጋጋሚ ጥረት ሳይሳካ ቀርቷል። የሲዳማ አርነት ንቅናቄ (ሲአን) ዋና ጸሀፊ አቶ ለገሰ ላንቃሞ ግን በሁላ የሞቱ ሰዎች ቁጥር 18 መሆናቸውን ማረጋገጣቸውን ለዶይቼ ቬለ ተናግረዋል። እስካሁን ከሲዳማ ዞን ሶስት የተለያዩ አካባቢዎች ባሰባሰቡት መረጃ የሞቱ ሰዎች ቁጥር 34 መድረሱንም ገልጸዋል።

“በሀገረ ሰላም ወይም በሁላ ወረዳ እስከ 18 ሞተዋል። በመልጋ 12 ሞተው ብዙዎች ቆስለዋል። የሞቱትን በትክክል አውቀናል፤ የቆሰሉትን ቁጥር በትክክል ማወቅ አልቻልንም። በሀዋሳ ላይ አራት ሰዎች እንደሞቱ ከተማ አስተዳደሩ ራሱ በመገናኛ ብዙሃን ቀርበው የተናገሩትን ነው። ሰባት ቆስለዋል፤ አራት ሞተዋል።  በአጠቃላይ ከ26 እስከ 30 ድረስ ይነገራል። በትክክል ግን ስናውቅ ነው አጠቃላይ መግለጫ የምንሰጠው።” ያሉት አቶ ለገሰ «ይርጋለም እና ለኩ፣ አለታ ወንዶ የሞቱትን አላገኘንም” ሲሉ አክለዋል።

የደቡብ ክልል ቴሌቪዥን ጣቢያ በዛሬው ምሽት ስርጭቱ በአለታ ወንዶ፣ አለታ ጩኮ እና ሀገረ ሰላም የደረሱ የንብረት ውድመቶችን አሳይቷል። ጣቢያው የደቡብ ክልል ርዕሰ-መስተዳደር አቶ ሚሊዮን ማቲዎስ፣ የሲዳማ ዞን አስተዳዳሪ አቶ ቃሬ ጫዊቻ እና የቀድሞው የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ደሴ ዳልኬ ሶስቱን ከተማዎች ተዘዋውረው ሲመለከቱ በምስል አስደግፎ ለዕይታ አብቅቷል።

ጉዳት የደረሰባቸው የከተማይቱ ነዋሪዎች እምባ እየተናነቃቸው የደረሰባቸውን ጉዳት ለባለስልጣናቱ ዘርዝረዋል። በቴሌቪዥን ጣቢያው የተቃጠሉ ፋብሪካዎች፣ ቤቶች እና መኪናዎች የታዩ ሲሆን የክልሉ ባለስልጣናትም የባለንብረቶቹን ባለቤቶች ሲያነጋግሩ እና ሲያጽናኑ ተደምጠዋል። የክልሉ መገናኛ ብዙሃን በተለያዩ የሲዳማ ዞን አካባቢዎች የሞቱ ሰዎች እንዳሉ ቢጠቅስም ቁጥራቸውን ሳይገልጽ አልፏል።

ተስፋለም ወልደየስ

እሸቴ በቀለ

**ቀን** 21.07.2019

**ርዕሰ ጉዳዮች** ኢትዮጵያ

**ቁልፍ ቃላት** ኢትዮጵያ, ሲዳማ, ሁላ ወረዳ, ሀገረ ሰላም, ሚሊዮን ማቴዎስ, ቃሬ ጫዊቻ, ደሴ ዳልኬ

**አስተያየትዎ**: ምላሽ

**ያትሙ** ገፁን ያትሙ

**Permalink** https://p.dw.com/p/3MTZN

## ከማዕቀፉ ተጨማሪ ዘገባዎች




### በአማራ ክልል በጃሪ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ተፈናቃዮች እሮሮ

23.05.2023

አማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን ተሁለደሬ ወረዳ በጃሪ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ተፈናቃዮች የምግብ እጥረት እንዳጋጠማቸው ተናገሩ። በአፈር ጥበቃ ስራ ተሰማርተው በቀን ይሰጣቸዋል የተባለው ገንዘብም እንዳልተከፈላቸው ተፈናቃዮቹ ገልፀዋል።




### የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስትያን አዲስ ኮሚቴ አቋቋመች

23.05.2023

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያን ቅዱስ ሲኖዶስ "ችግር ባለባቸውና እና አስፈላጊ በሆኑ አኅጉረ ስብከቶች" ዘጠኝ አዳዲስ ኤጴስ ቆጶሳትን ለመሾም ሰባት አባላት ያሉት አስመራጭ ኮሚቴ መሰየሟን አስታወቀች።ሲመተ ጵጵስናው የሚከናወንበት ቀን እና ሁኔታ ወደፊት ይገለፃል ብላለች።




### የሰላም ስምምነቱ ትግበራ ቅኝት በትግራይ

22.05.2023

የትግራይ ኃይሎችን ከ85 እስከ 90 በመቶ የሚሆን ትጥቅ የማስፈታት ሥራ መፈፀሙን በአፍሪካ ሕብረት የሰላም ስምምነቱ ተቆጣጣሪ ልዑክ ገለፀ።



© 2023 Deutsche Welle | የግለሰቦች/ድርጅቶች ሰነድ ጥበቃ | የተደራሽነት መግለጫ | Legal notice | አድራሻ | ለሞባይል የተዘጋጀ

ለርስዎ የምናቀርበውን አገልግሎታችንን ለማሻሻል በማሰብ ኩኪዎችን እንጠቀማለን። ስለዚሁ ጉዳይ ተጨማሪ መረጃዎችን ከሰነድ አጠባበቅ መግለጫችን ማግኘት ይችላሉ።

ተጨማሪ መረጃዎች | እሺ